# እኛነታችን

ተዘራ አሰጉ / ከምድረ እንግሊዝ /

እኛነታችን በተምሳሎተ ባህል ተጋምዶ
ኢምንት ልዩነታችን ተዛምዶነቱ ልቆ ፤

የኖርንበት ያማርንበት ለዘመነ ዘመናት
አሸበረቀ አጎመራ ተወራርሰን ስንዘልቅበት ፤

ልዩነታችን ከጥንት ከመሰርቱ
መኩሪያ የጋራ ሃብታችን ህብሩ ፤

ኢትዮጵያዊ መልኩ
እንዲሉ ነብር ዥንጉርጉረነቱ ፤

ቃሉ ሲናገር መሰረተ ዉሉ
ሁላችን  አንድ ነን ከጥንቱ ፤

ደቡብ ሰሜን ቢያቋርጡ
ወደ ምስራቅ ምሕራብ ቢዘልቁ ፤

ኢትዮጵያዊነት ድባባችን ግማዱ
ከአንድ ዘር ግንድ የወጣ ይዕትብታችን ስሩ ፤

የሰሜኑ "ዕልበቱ " "ስቅስቆ" ወጡ
የደቡብ "ክትፎው" "ቆጬው" ጥዑሙ ፤

የምዕራቡ ቡና ያፈላል ስርዓቱ
የምስራቅ "ስፌት" ዕደ ጥበቡ ፤

የኛነታችን የጋራ መገለጫችን ቱፊቱ
ስናምር ታጋርተን ስኖርበት በወሉ ፤

ስናርስም አንድ ስንዘራ
ስናጣምድ ቃንጃ በሬ በአንድ መላ ፤

ስናዋድር ሞፈሩን ከቀምበሩ
ልንካፋል አንድ ሆነን ከመከሩ ።

እሰየው የኢትዮጵያ ልጆች ሲያምሩ
በአንድ ሲተሙ ሲጋመዱ ሲዋደዱ ።

ኢሚንት ልዩነታቸው
"ደሃን" "ደህና" ሲባባሉ ።

ከየት ነበርክ ከየት መጣህ ሲባባሉ
"ከጉራጌ - ከጉራ" ከቅርብ ከአፋፉ ።

"ኦቦ" "ኣባ" ሲባባሉ
ቃሉ አንድ ዘይገርም በሉ ።

ዛሬማ ዘመኑ ላቅ ብሎ
ሳይንሱ ረቆ ነጉዶ ።

መንገዱ አስፓልቱ ተጠርጎ
ረቡላ ባቡሩ ሊዘረጋ አኮብኩቦ ።

ግድብ መብራቱ ቀንና ሌቱን አድምቆ
እሸትና መጎሩን ባንድ ማድ ሊቋደሱ ቀርቦ ።

ኪናዊ ጥበባቸው በአንድ መድርክ ተወድሶ
ስናዜም ጨቤ ስንረግጥ ተመሳስሎ ።

ቡናው ፈልቷል "ነይ" "ንኢ" ሲባባሉ
ክትፎዉ ሳይብርድ ተጠራርተው ሊቋደሱ ።

የደብቡ የወላይታው ውዝዋዜ መስህቡ ።
ከአገው ከአማራው እስክስታ ተምሳሎቱ ።

የአደሬው ውዝዋዜ አረጋገድ
ከትግራዮ መመሳሰል ሽረር-ሽረር ።

የኦሮሞው የኩናማው የሱማሌ ጭፈራ ዳንስ
ትስስሩ ከቤንሻጉል ፤ ከአፋሩ  ከጋምቤላው ፤

ያራራቀን ደንቀራ ተሰባብሮ
የወንድም እህትነት ፍቅራችን አጎምርቶ ፤

የአንዱን ባሕል ሌላው ወገን ሊኖርበት
ሊያጌጥበት ሊላበሰው ሊኮራበት ፤

የአማራ የደቡብ ልጆች
የኦሮሞ የቤንሻጉል ጉብሎች፤

የጋምቤላ የሃፋር ፈርጦች
የሱማሌ የሐረር ውቦች ፤

አንድ ሆኑ ተጋመዱ ተዋደዱ
ተከባብረው በኢትዮጵያዊነት መቀነት ተቋጠሩ ፤

እልል ደስ ይበልሽ ኢትዮጵያ ሃገሬ
ሰንደቅሽ አበራ በሕዝብሽ ዝማሬ ፤

አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዴራሽ
በብሔር ብሄረሰብ ግማድ አሸበረቀልሽ ።

ተዘራ አስጉ ከምድረ እንግሊዝ